# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የተጋባዥ ተዋንያን የመድረክ ክፍያና የልምምድ አበል መመሪያ ቁጥር 61/2013

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትጠቀስበት የቆየው ድህነትና ኋላቀርነት በአሁኑ ወቅት እየተቀየረ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት ከሚያስመዘግቡ ሃገራት ጋር እየተጠራች ትገኛለች፡፡ ይህ ኢኮኖሚያዊ እድገት እዉን የሚሆነው ቀጣይነት ካለው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ልማት ጋር ሲቀናጅ ነው፡፡ በመሆኑም ልማት ሁሉን አቀፍና የተቀናጀ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ስለዚህ ነው መንግስት በየዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችን ነድፎ እየሰራ የሚገኘው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ለባህልና ኪነጥበብ የፖሊሲ ድጋፍ በማድረግ የሀገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህል፣ ትውፊት እና ታሪክ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያገኙ የተቻለዉን እያደረገ ይገኛል፡፡<< ኢኮኖሚያዊ እድገት ያለማህበራዊ ልማት ብቻዉን ዘላቂነት አይኖረዉም>> የሚለዉን መርህ በመከተል መንግስት ለባህልና ስነጥበብ ድጋፍ እያደረገ ነው፡፡ በሂደትም በየዘርፉ ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት ልዩ ልዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ አንዱ የባህል አምባሳደር ለሆኑት የኪነጥበብ ባለሙያዎች ክብራቸዉን የሚመጥን የሙያ ማበረታቻ ክፍያ እንዲያገኙ መንግስት የተቻለዉን ሁሉ እያደረገ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር በ2003 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ማስረት የተሰጡትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተጋባዥ ተዋንያንን የመድረክ ክፍያናየልምምድ አበል ማሻሻል አስፈላጊነቱን ከታች በተዘረዘሩት ነጥቦች፡-

1. የኪነጥበብ ሙያተኞች ለሙያው ፍቅር ሲሉ ብቻ እየተጎዱ በመቆየታቸው የተነሳ ቀስ በቀስ ከሙያው የራቁትን ለመሳብ፡፡
2. በየጊዜው እየናረ የመጣዉን የኑሮ ወድነት በማጡም ቢሆን እንዲቋቋሙ ለማገዝና ሙያተኞችን ለማበረታታት፡፡
3. በጡረታና በልዩ ልዩ ምክንያት ከቴአትር ቤት ወጪ ያለዉን እዉቀጥ ክህሎት ልምድና ተሰጥኦ ሽግግር ለማጠቀም፡
4. የቴአትር ቤቱ መግቢያ ዋጋ ጨምሮ የተጋባዥ ሙያተኛው ገቢ በዚያው መቀጠል ስለሌለበት፡፡
5. ቀደም ሲል ይሰራበት የነበረው የተጋባዥ ተዋንያን ክፍያ ተመን ባለሙያዎችን የሚያበረታታ ባለመሆኑ የማሻሻ ያ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

### አንቀጽ 1

### አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ << የኢትዮጵያ ብሐየራዊ ቴአትር የተጋባዥ ተዋንያን የመድረክ ክፍያና የልምምድ አበል መመሪያ 61/2013>> ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 2

## ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ

1. << ተጋባዥ ተዋናይ ማለት >> በቴአትር ቤቱ ወስጥ መደበኛ ሰራተኛ ያልሆነ በተወኔት ወስጥ ወየም በሚዚቃዊ ተወኔት ወስጥ በችሎታው ወይም በተሰጥአው ምክንያት አንድን ገጸባህሪ ለሚጫወት እና ለዚያ ስራ ብቻ የዋለ ባለሙያ ማለት ነው፡፡
2. << ልዩ ተጋባዥ ተዋናይ >> ማለት በስራ ወጤቱ የተማከረለት ከፍተኛ ችሎታ እወቀት እና ልምድ ያለው አንጋፋ ወይንም ላቅ ያለ ዝና ያለው አርቲስት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በተለያየ ምክንያት አዘወትሮ በመድረክ ላይ የሚይቀርብ ተዋናይ ማለት ነው፡፡
3. << የመድረክ ክፍያ>> ማለት አንድ ተዋናይ የተለማመደወን ቴአትር በመድረክ ላይ በሚያቀርብበት ጊዜ የሚከፈለው የሙያ ክፍያ ነው፡፡
4. << የልምምድ አበል>> ማለት አንድ ተዋናይ የቴአትሩን ዝግጅት በሚለማመድበት ወቅት ለአንድ ሙሉ ቀን ልምምድ የሚከፈለወን አበል ማጠን የሚገልጽ ነው፡፡
5. << የቴአትር ዝግጅት >> ማለት የቴአትር ፣ሚዚቃዊ ድራማና አጭር ድራማ ዝግጅትን ያጠቃልላል፡፡
6. << ዳይሬክቶሬት >> ወይም << የስራ ሂደት>> ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የስራ እንቅስቃሴ ወስጥ ወጤት ለማምጣት ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑበት ተያያዥነትና ተከታታይነት ያላቸው ተግባራት ከመነሻ እስከ መድረሻ የሚከናወኑበት የአንድን ክፍል ስራ ፍሰት የሚያሳይ አደረጃጀት ነው፡፡
7. << ኮሚቴ >> ማለት ተጋባዥ ተዋንያንን በሚመለከት ለስራ የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ለማስራት /ለማስፈጸም/ የተደራጀ ሂደትን የባለሙያ ቡድን ነው፡፡
8. << የሙያ ብቃት>> ማለት የሚጠበቀወን ወጤት ለማግኘት የሚያስፈልገወን እወቀት ክህሎትና ዝንባሌ የሚመለከት ነው፡፡
9. << አዘጋጅ>> ማለት ለዘጋጅ የተፈለገወን ቴአትር ወይም ሚዚቃዊ ድራማ ባው የፈጠራ ሙያ ችሎታ እና ልምድ ለጥበባዊ ወጤት የሚያበቃ ባለሙያ ነው፡፡
10. << የበላይ አሜራር/ኃላፊ>> ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትርን በበላይነት ለመምራት በመንግስት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር እና በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኝ ኃላፊ ነው፡፡
11. << የስራ አሜራር>> ማለት በቴአትር ቤቱ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የተለያየ ወሳኔ የሚያስተላልፍ የስራ ኃላፊዎች ስብስብ ማለት ነው፡፡
12. ማንኛወም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## አንቀጽ 3

## ዓላማ

1. የመመሪያው ዓላማ ቴአትር ቤቱ ለሚያዘጋጃቸው መደበኛ ቴአትሮች ትወፊታዊ ታሪካዊ ዘመን አይሽሬ ልማታዊና የማሰሉት ቴአትሮችና ድራሞዎች ዝግጅቶች ላይ ችሎታ እወቀት ክህሎት ያላቸወና በህዝብ ዘንድ በሙያቸው ታዋቂና ዝና ያላቸወን ተዋንያን ማሳተፍ፡፡

2. በቴአትር ቤቱ ባለሞያዎች ብቻ ለሰሩ የሚይቻሉትን ገጸባህሪያት በደንብ ሊጫወቱ የሚችሉ አንጋፋ ወጣትና ህጻን ተዋንያንን ለማስተፍ የሚያስችል የሞያ ክፍያወን ማጣጣምና ማሻሻል፡፡

## አንቀጽ 4

## የአሰራር መርሆችና ሂደቶች

1. የተጋባዥ ባለሞያው ችሎታ ልዩ ተሰጥኦ የህዝብ ተቀባይነት እና የስራው ሃገራዊ እና ልማዊ ፋይዳ ታይቶ እንዲጋበዝ ይደረጋል፡፡
2. ባለሞያዎችን እንደ ችሎታቸው የህዝብ ተቀባይነታቸው እንደተሰጣቸው ሜ ክፍያ ይፈጸማል፡፡
3. የተጋባዥ ባለሞያ ጥያቄ የሚቀርበው ለዘጋጅ ለታሰበው የፈጠራ ስራ በተመደበው አዘጋጅ በኩል ነው፡፡
4. የተዋናይ ተጋባዥ ለመጥራት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፡-
   ሀ. አዲ ዝግጅት ሲኖር እና ዝግጅቱ የሚያስፈልገወን ችሎታ እና ተሰጥኦ ለማሟላት
   ለ. ትርኢቱ በመደበኛነት እየቀረበ ባለበት ወቅት የባለሞያ መጓደል ሲያጋጥም
   ሐ. የባለሞያ መጓደል አጋጥሞ በቅጥር መተካት ሳይቻል ሲቀር
   መ. የቴአትር ተሜካቾችንና ደንበኞችን ጥያቄ (ፍላጎት) መሰረት በማድረግ
5. ለተዋናይ ተጋባዥ ለመሆን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፡-
   ሀ. ይቀርባል ተብሎ በሚታሰበው ወይም በሚቀርበው ትርኢት ወስጥ የሚያስፈልገወን ችሎታ ተሰጥኦ ልምድ ትጋትና የህዝብ ተቀባይነት አሟልቶ ሲገኝ
   ለ. ቴአትር ቤቱ በተመለተ የክፍያ እርከን ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ
   ሐ. ቴአትር ቤቱ ለትርኢቱ የተያዘለትን ፕሮግራም ለማጠናቀቅ ፈቃደኛ የሆነ
   መ. የሞያ ስነምግባር ያለው
6. ተዋንያንን ለመጋበዝ መሟላት ያለባቸው ሂደቶች

   ሀ. ዝግጅቱን ከሚያዘጋጁ አካላት የተፈለገወን ተጋባዥ የሚጠይቅ ማጠየቂያ

   ለ. ዝግጅቱ ከሚገኝበት ንኡስ የስራ ሂደት (ዳይሬክቶሬት ) የስምምነት መግለጫ

   ሐ. ዝግጅቱ ከሚገኝበት ዳይሬክቶሬት በዳይሬክተር የሚመራ የተጋባዥ የኪነጥበብ ባለሞያዎች ክፍያ የወሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሜቴ በቃለ ጉባኤ የሰፈረ የወሳኔ ሃሳብ

   መ. አስፈላጊ ነገሮችን አሟልቶ የወሳኔ ሃሳቡን አቅርቦ በዋና ዳይሬክተር ማጽደቅ

   ሠ. ዝግጅቱ የሚገኝበት የስራ ሂደት ከተጋባዥ ባለሞያ ጋር ወል ሚፈጸም፡፡

7. የተጋባዥ ተዋንያን የመድረክ ክፍያ የወሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት
   ሀ. ኮሚቴው የሚመራው ዝግጅት በሚገኝበት የስራ ሂደት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ይሆናል፡፡
   ለ. ከዝግጅቱ አካል አስተባባሪው ወይም ረዳት አዘጋጁወይንም አዘጋጅ የኮሚቴው አባል ይሆናል
   ሐ. ኮሚቴው በሶስት አባላት ይዋቀራል፡፡ አወቃቀሩም ዝግጅቱ የሚገኝበት የስራ ሂደት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሰብሳቢ ከዝግጅት ክፍሉ ጸሃፊ እና ከቴአትር ዋና አዘጋጅ አባል ይኖሩታል፡፡
   መ. ኮሚቴው በዚህ መመሪያ በተገለጹት ሁኔታዎች እና በተመኖቹ ገደብ መሰረት የተጋባዥ ተዋንያንን የክፍያ ተመን የወሳኔ ሃሳብ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፡፡

ሠ. ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

8. በሚበኛትርቶች ላይ ለሚሳተፉ ተጋባዥ ባለሞያዎች ወር በገባ በአምስት ቀናት ወስጥ የሰሩበት ክፍያ ይፈጸማል፡፡

9. ልዩ ሁኔታዎች፡-

ሀ. የቴአትር ቤቱ ዋና ዳይሬክተር የወቅቱን ሁኔታ በማገናዘብ የተጋባዥ ባለሞያዎችን ቁጥር ሊወስን ይችላል፡፡

ለ. የተጋባዥ ባለሞያዎች ቁጥር ብዘት ካለው የቴአትር ቤቱ የበላይ አሜሩር ማስተካከያ ሊደረግ ይችላል፡፡

ሐ. በልዩ ሁኔታ ተጋባዥ ተዋናዩ የሚሰራበት የተለየ ጥያቄ ሲቀርብ የቴአትር ቤቱ የስራ አሜሩር ጉዳዩን በመጥጫ በድርድር የሚሰራበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይችላል፡፡

መ. የቴአትር ቤቱ የስራ አሜሩር ጥርጣሬ ሲኖረው በተጋባዥ ባለሞያ አሜሩረጥ ላይ ጣልቃ ሊገባ ይችላል፡፡

ሠ. ጠያቂው አካል ቅድሚያ ዳሰሳ ጥናት በማድረግ የቴአትር ቤቱን ደረጃ የሚመጥኑ ባለሞያዎችን በማሟረጥና በመመዝገብ ለበላይ አሜሩር ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ 5

### 5.1 የተጋባዥ ተዋናይ የመድረክ ክፍያና የልምምድ አበል ተመን

| ተ.ቁ | ደረጃ | ክፍያ | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1. | 1.1 ልዩ ተጋባዥ ተዋናይ | | |
| | | በልዩ ሁኔታ የሚወሰን | 1. ለትወና ላቅ ያለ ችሎታ እና ዝና ያለው አንጋፋ ወይም ታዋቂ የሆነና በአሁኑ ወቅት አዘውትሮ በመድረክ ላይ የሚገኝ ተዋናይን ብቻ ይመለከታል፡፡<br>2. ከመድረክ ቴአትር በተጨማሪ በሬዲዮ ድራማ በቴሌቪዥን ድራማ ወይም በፊልም ተዋናይነት ታዋቂ መሆን አለበት<br>3. በስራ ዘመኑ ያካበተውን የሞያ ልምድና ስነምግባር ለሌሎች ሊያካፍል የሚችል ባለሞያ መሆን ይኖርበታል፡፡<br>4. እንደ ገጸባህሪው የስራ ክብደት ጥያቄው ከዝግጅት ክፍሉ ቀርቦ በቴአትር ዳይሬክቶሬት ከተረጋገጠ በኋላ በስራ አሜሩር ሲጸድቅ ብቻ ተጋባዥነቱ የሚጸና ይሆናል፡፡ |
| | 1.2 መደ ተዋናይ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሜ ተዋናይ I | ብር 500.00 | ሜ ወይም ወስብስብ ገጸባህሪ የሚጫወትና በትወና ከፍተኛ ዝና ያለው ተዋናይ |
| | ሜ ተዋናይ II | ብር 350.00 | ሜ ወይም ወስብስብ መካከለኛ ገጸባህሪ የሚጫወትና በትወና መካከለኛ ዝና ያለው ተዋናይ |
| | ሜ ተዋናይ III | ብር 200.00 | ሜአከላዊ ገጸበባህሪ የሚጫወትና በትወና ጀሜ ወይም አነስተኛ ልምድ ያለው |
| | አጃቢ ተዋናይ | ብር 75.00 | በትወና ልምድ ያለውም ሆነ የሌለው ሆኖ አጃቢ ገጸባህሪያትን የሚጫወት |
| 3 | ለአጭር ድራማ | | |
| | ሜ ተዋናይ I | ብር 250.00 | በትወና መካከለኛ ዝና ያለው ሆኖ ሜ ገጸባህሪን የሚጫወት |
| | | | |
| | አጋር ተዋናይ II | ብር 150.00 | በትወና ጀሜ ወይም ሜአከላዊ ልምድ ያለው ሆኖ ሜአከላዊ ገጸባህሪን የሚጫወት |
| | አጃቢ ተዋናይ | ብር 100.00 | በትወና አነስተኛ ልምድ ያለው ሆኖ አነስተኛ ገጸባህሪያትን የሚጫወት |
| 3. | የልምምድ አበል | | |
| | ለተጋባዥ ተዋናይ | ብር 40 | ለማንኛውም ተጋባዥ ተዋናይ ብቻ በተለማመዱባቸው ቀናት ብቻ ለአንድ ሙሉ ቀን የሚከፈል |

### 5.2 ልዩ ማለጫ

5.2.1 ከላይ የተገለጹት ክፍያዎች የሚፈጸሙት ለቴአትር አገልግሎት ብቻ ይሆናል

5.2.2 ይህ መመሪያ በስፖንሰር ድጋፍ ሰጪዎች በፕሮጀክት ወይም በሌላ የፈጠራ ስራ ሜልክ የሚሰራስራን ክፍያ አያካትትም

## አንቀጽ 9
## መመሪያውን ስለማሻሻል

በዚህ መመሪያ ወስጥ የተደነገጉ ጉዳዮች ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ሲታመንበት መመሪያው ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 10
## መመሪያውን አለሚፈጸም የሚያስከትለው ተጠያቂነት

1. ይህ መመሪያ አለሚፈጸሙ ሲረጋገጥ መመሪያው እንዳይፈጸም ባደረገው አካል ወይም ግለሰብ ላይ አግባብ ባለው የመንግስጥ ሰራተኛ አዋጅ ደንብና የሲቪል ሰርቪስ መመሪያዎች መሰረት እንደ ጥፋቱ ሁኔታ እየታየ ቀላልና ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ሊወሰን ይችላል፡፡
2. በዚህ መመሪያ የተደነገገውን በማወቅ ወይም በቸልተኝነት ያልፈጸመ ማንኛውም ኃላፊና ሰራተኛ በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 67-70 ባሉት እና በፌደራል መንግስት ሰራኞች የዲሲፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት ደንብ ቁጥር 77/94 መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3. ቀላልና ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚወሰነው ኃላፊው ወይም ሰራተኛው ወይንም ተጋባዥ ባለሞያው ተጸጽቶ እንዲታረምና ብቁ ሰራተኛ እንዲሆን ለማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማስናበት ነው፡፡

## አንቀጽ 11

## መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሀሴ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ተስፋዬ ሽመልስ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ዋና ዳይሬክተር